| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ብሔረ ፡ ጥበብ ። " |
| ርእስ ፤ | "ምድርና ፡ ኅዋ ።<br>ክፍል ፡ 2 ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ግንቦት ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-002 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ብሔረ ፡ ጥበብ ።

Universe of Science | Univers de la science

# ምድርና ፡ ኅዋ ።

## ክፍል ፡ 2 ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ።

ምድራችን ፡ ራሷን ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ ዘንበል ፡ አድርጋ ፡ በማይለወጥ ፡ ዝግመት ፡ ከምዕራብ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የምትሽከረከርን ፡ እንዝርት ፡ ትመስላለች ። በራሷ ፡ ላይ ፡ እየተሽከረከረች ፥ በማይለወጥ ፡ **ምሕዋርም** ፡ (circuit) ፡ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ ታውዳለች ።

በራሷ ፡ አንድ ፡ ዙር ፡ ለመዞር ፡ 24 ፡ ሰዓት ፡ ይፈጅባታል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፥ የፀሓይ ፡ ብርሃን ፡ ባገኘው ፡ የምድር ፡ ግጽ ፡ መዓልት ፡ ወይም ፡ ቀን ፡ ይኾናል ፤ ባላገኘውና ፡ በጨለመው ፡ ደግሞ ፡ ሌሊት ፡ ይኾናል ። በፀሓይ ፡ አንጻር ፥ እንደ ፡ ምድሪቱ ፡ ዝንባሌ ፥ የመዓልትና ፡ የሌሊት ፡ ሰዓት ፡ ካ 12 ፡ ሰዓት ፡ ዝቅ ፡ ወይም ፡ ላቅ ፡ ይላል ።

ምድር ፥ በራሷ ፡ እየተሽከረከረች ፥ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ የምታውድበት ፡ **ዑደት** ፡ (orbit) ፡ 365 ፡ ቀን ፡ ከሩብ ፡ ይፈጅባታል ፤ ይህንም ፡ 1 ፡ ዓመት ፡ እንለዋለን ። አንዱ ፡ ዓመት ፡ ተራውን ፡ በወራት ፡ ይከፈላል ። በኢትዮጵያ ፡ የዘመን ፡ አቈጣጠር ፥ ዓመቱን ፡ ባ 12 ፡ ባለ 30 ፡ ቀናት ፡ ወራት ፡ (መስከረም ፣ ጥቅምት ፣ ኅዳር ፣ ታኅሣሥ ፣ ጥር ፣ የካቲት ፣ መጋቢት ፣ ሚያዝያ ፣ ግንቦት ፣ ሠኔ ፣ ሐምሌ ፣ ነሐሴ) ፡ እና ፡ ባ 1 ፡ ባለ 5 ፡ ወይም ፡ 6 ፡ ቀናት ፡ ወር ፡ (ጳጕሜ) ፡ እንከፍለዋለን ።

ለፀሓይ ፡ የቀረበው ፡ የምድር ፡ **ወገብጌ** ፡ (equator) ፡ የሚሞቀውን ፡ ያኽል ፥ ለፀሓይ ፡ የራቁት ፡ ሰሜናዊውና ፡ ደቡባዊው ፡ ዋልታዎች ፡ አርክቲክና ፡ አንታርክቲክ ፡ ዓመት ፡ ከዓመት ፡ ግግር ፡ በረዶን ፡ ይለብሳሉ ። ከኹለቱ ፡ መኻከል ፡ የሚገኘው ፡ ክፍል ፡ ከቀዝቃዛ ፡ እስከ ፡ ሞቃት ፡ አየርን ፡ ያስተናግዳል ። ከዚህ ፡ ጋራ ፥ እንደምድር ፡ ዝንባሌና ፡ እንደምሕዋሩ ፡ አካባቢ ፥ የአየር ፡ ንብረቱ ፡ ስለሚለውጥ ፥ እስከ ፡ አራት ፡ የሚደርሱ ፡ **ብሬቶች** ፡ (seasons | saisons) ፡ ይታያሉ ። እነዚህም ፡ መፀው ፡ (መከር) ፣ ሐጋይ ፡ (በጋ) ፣ ጸደይ ፡ (በልግ) ፣ ክረምት ፡ ይባላሉ ። ባንዳንድ ፡ አካባቢ ፡ ደግሞ ፡ ክረምትና ፡ በጋ ፡ ኾነው ፡ ለኹለት ፡ ይከፈላሉ ።

በምድር ፡ ውስጣውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ አስኳል ፡ የቀለጠ ፡ ብረት ፡ በመኾኑ ፥ የምድር ፡ መሽከርከር ፡ ብረቱን ፡ እንደ ፡ ፈልቅ ፡ ወይም ፡ ማግኔት ፡ ስለሚያደርገው ፥ በ**መርሐ** ፡ **ሰሜን** ፡ (compass | boussole) ፡ ለመመራት ፡ ይፈቅዳል ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።